በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትምህርት ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የትምህርት ሚኒስቴር የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት መ/ቤቱ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደብዳቤ ቁጥር 24/1-533/2589/35 በቀን 24/01/2010 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ ሪፖርት የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በመ/ቤቱ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፤
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፤

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፤

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. **የወጪ ሂሳብን በተመለከተ፤**
    1. የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል ሰኔ 2004 ዓ.ም በወጣው የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-መ/ቤቱ በሃገራችን ባለው የመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮች አሰለጣጠን ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከኮሌጆች ለተውጣጡ 15 ባለሙያዎች የተቋቋመ የጥናት ግብረ ሀይል የመጀመሪያው ዙር ለ20 ቀን በአራራት ሆቴል ጥናቱ ሲካሄድ፤ ከብሪቲሽ ካውንስል ከሚገኘው ድጋፍ የሚተካ በሚል ለውሎ አበልና ለሙያ አበል ብር 478,200.00 ክፍያው ከመደበኛ በጀት የተፈፀመ ሲሆን በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው ቀጥታ ወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤
    2. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ላዘገዩበት ጊዜ

ሳይፈጽሙት በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡- መ/ቤቱ የኤሌክትሮኒክስና የቢሮ ጥገናና ተዛማጅ እቃዎች ግዥ ለመግዛት ባወጣው ግልጽ ጨረታ ኤን ኤም ኤች ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር በማሸነፍ በብር 636,725.00 በቀን 20/07/2009 ውል የያዘ ሲሆን በውሉ መሰረት እቃዎቹን በ15 ቀን ውስጥ ማለትም እስከ 05/08/2009 እንደሚያስገባ ውል የያዘ ቢሆንም እቃዎቹ ገቢ ያልሆኑበት ምክንያት አሳማኝ ማስረጃ ሳይኖር መግባት ከነበረበት ቀን ከ35 ቀናት በኋላ በ10/09/2009 ገቢ የሆነ በመሆኑ ድርጅቱ ላዘገየበት የጉዳት ካሳ በመመሪያውና በውሉ መሰረት ከጠቅላላ ውል ብር 22,285.06 (636,716.26*1/1000*35) መቀጣት ሲገባው ምንም አይነት የጉዳት ካሳ ያልከፈለ መሆኑ፤

3. መ/ቤቱ ለከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን ለመግዛት የሚያማክር የግዥ አማካሪ ለመቅጠር በ25/02/1998 በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በግልጽ ጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈው የግዥ አገልግሎት ድርጅት በቀን 14/01/1999 በብር 2,983,757.20 ለመስራት ውል ተፈራርሞ ስራውን ከጀመረ በኋላ የስራው 50% ክፍያ ተፈፅሞለት በ22/10/2003 ውሉ ተቋረጠ፡፡ ሆኖም ስራው 80% ስለደረሰ ቀሪው 30% ብር 963,577.48 ሊከፈለኝ ይገባል በማለት እንዲከፈለው በተደጋጋሚ በመጠየቁ፤ የመ/ቤቱ ሚኒስትር ዴኤታ በቀን 16/04/2007 በቁጥር 7/260/1349/07 ለድርጅቱ ቀሪውን ብር በጠየቀው መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የታዘዘ ከመሆኑ በተጨማሪ የመስሪያ ቤቱ የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በ22/03/2007 ለሚኒስትሩ ቢሮ ኃላፊ በተጻፈ ማስታወሻ የውሉን 80% ያጠናቀቀ ከሆነ ድርጅቱ የጠየቀው ቀሪ 30% ክፍያ እንዲከፈለው ቢደረግ የተሻለ መሆኑን ምክንያቱም ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ቢሄድ የማያዋጣ እና መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳርግ ከማድረጉ በተጨማሪ ከተቋሙ ጋር ያለውን የመልካም ስራ ግንኙት እንዳያሻክር ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል አስተያየት የሰጠ ቢሆንም መ/ቤቱ ክፍያውን ሳይከፍል በመቅረቱ ድርጅቱ ክስ በመመስረቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 13/01/2009 በዋለው ችሎት ከተቋረጠበት 14/10/2003 ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በጠቅላላው 5 ዓመት ከ7ወር ያልተከፈለውን ብር 963,577.48 እና 9% ህጋዊ ወለድ ብር 484,197.68 በድምር ብር 1,447,775.15 በፍርድ ቤቱ በመወሰኑ መ/ቤቱ አላግባብ ብር 484,197.68 በክትትል እና የአሰራር ችግር ምክንያት ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል ተደርጓል፡፡

4. በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ፤ እንዲሁም ሰኔ 2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በዚህ መሠረት ለመስራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በግልጽ ጨረታ መፈጸም የነበረበት በድምሩ የብር 1,780,791.68 ግዥ ያለምንም ውድድር በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ መገኘቱ፤
5. በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ለክፍያው ትክክለኛ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፣ ሚሲዮኖችና እና በዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ በትክክል ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምር ብር 157,383,533.13 ክፍያ በመፈጸም በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

6. በፌዴራል መንግሥት የግዥ መመሪያ ሰኔ 2003 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 16.26 ቁጥር 1 በመንግሰት ግዥ አፈጻጸም እንደ አስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30% /ሰላሳ/ የሚደርስ ቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል ይላል፡፡ ነገር ግን የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታና መሰረተ ልማት እስከ ሰኔ 30/2009 ለኦዲት በቀን 12/12/2009 በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መሰረት የኦዳቡሉቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ለማከናወን ከ11 ህንጻና የግንባታ ስራ ተቋራጮች ጋር በቀን 20/08/2008 እና ከአንድ የመሰረተ ልማት ተቋራጭ ጋር በቀን 05/07/2009 ውል የተያዘ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ የሚውል የቦታ ርክክብ ሳይደረግና ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባበት አካባቢ ላሉ ተነሺዎች የካሳ ግምት ሳይቀርብና ካሳ ሳይከፈላቸው አስቀድሞ ውል ከመያዙ በተጨማሪ የህንጻ የስራ ተቋራጮች የቦታ ርክክብ

ሳያደርጉና ወደ ስራ ሳይገቡ ቅድመ ክፍያ ለ9 ኮንትራክተሮች የዋናውን ውል 20% በ2008 በጀት ዓመት በድምር ብር 40,594,366.64 ከአንድ ዓመት በላይ እና ለአንድ ኮንትራክተር በ2009 15% ብር 31,442,798.11 ከሶስት ወር በላይ ምንም ዓይነት ስራ ሳይሰራ የተከፈለ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 በድምር ብር 72,037,164.75 የመንግስት ገንዘብ በህንጻ ግንባታና መሰረተ ልማት ስራ ተቋራጭ ድርጅቶች እየተጠቀሙበት መሆኑ፤

7. በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የኮንትራት ሠራተኞች በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ሳይመደቡ ወይም ዘላቂነት ከሌለው የሥራ መደብ ላይ ሳይሰናበቱ እና በመ/ቤቱ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ሳያስፈቅድ በ2009 የሰው ሃብት አስተዳደር ለኦዲት በሰጠው የኮንትራት ሰራተኞች ዝርዝር መግለጫ መሰረት ለ5 ሰራተኞች ብር 214,116.00 ከመመሪያ ውጭ ለኮንትራት ቅጥሮች ተከፍሎ መገኘቱ፤

2. <u>የተሠብሣቢ ሂሣብ በተመለከተ</u>፤

1. የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ቁጥር 4/ሀ-ሰ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ላይ፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ብር 67,156,467.64 ከ 1 ዓመት እስከ 15 ዓመት ድረስ የቆየ የተሰብሳቢ ሂሳብ ያለ ሲሆን በተሰብሳቢነት ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ ብር 41,478,232.69 ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ የሚታይ ሲሆን ከማን እንደሚሰበሰብ እና በትክክል የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ የሌለው መሆኑ፤
2. በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አየያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል ሀ እና ለ ላይ የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሂሳብ ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበትና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው የአጠቃላይ የሂሳብ ሌጀር ሚዛን ወደ ገቢ፣ ወጪ፣

ዝውውር፤ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ በትክክል መተላለፍ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመመሪያው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በበጀት ዓመቱ በ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ /detailed transaction/ ላይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምር ብር 822,952,048.44 ሲሆን በዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የተደረገ የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምር 666,503,982.29 በመሆኑ የበጀት ዓመቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት በብር 156,448,066.15 (822,952,048.44 - 666,503,982.29 = 156,448,066.15) ዝቅ ብሎ (understate) ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤

3. <u>የተከፋይ ሂሣብን በተመለከተ</u>

የተከፋይ ሂሳቦች በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከሀ-ሠ በተዘረዘረው መሠረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በመ/ቤቱ ከ2001 እስከ 2009 በጀት ዓመት ጀምሮ የቆየ ብር 4,724,478.22 እና የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ብር 4,433,587.47 በድምር ብር 9,158,065.69 ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

4. <u>የበጀት ሂሣብ በተመለከተ፤</u>

ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ለየበጀት አርእስቱ ከተመደበው የካፒታል በጀት ብር 349,561,836.61 ከተደለደለው በጀት በላይ ጥቅም ላይ ውሎ ተገኝቷል፡፡

ከላይ በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴሩ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤</u>

- ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደለት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት የ12 ወር የበጀትና የወጪ አፈጻጸም ንጽጽር በየበጀት አርእስቱ ከ10% በላይ ሲታይ ከመደበኛ ብር 20,272,459.61 እና ከካፒታል ብር 254,268,290.98 በድምር ብር 274,540,750.59 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፡፡
- ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ለየበጀት አርእስቱ ከተመደበው የካፒታል በጀት ብር 278,210,628.39 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በአላቂ እቃዎች መጋዘን ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የፕሪንተር ቀለሞች፣ እስኪር ወረቀት፤ መጠረዣ /ሪንግ/ ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመት በላይ መቀመጣቸው፤
- የፍሬንና የሞተር ዘይት ከአላቂ ዕቃዎች‹ጋር በአንድ ክፍል ተቀላቅሎ መገኘቱ;
- በቁጥር የማይታወቅ በጣም ብዛት ያላቸው ኮምፒውተሮች፤ ፕሪንተሮች፤ ፎቶከፒ ማሽኖች፤ ፋይል ካቢኔቶች፤ ጠረጴዛዎች፤ ወንበሮች፤ የተሽከርካሪ ጎማዎች እና ሌሎችም ቋሚ እቃዎች በተለያዩ ክፍሎች ታሽገው የተቀመጡ በመሆኑ ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፡
- የተሰባበሩ የሽንትቤት እቃዎች፤ የተለያዩ ብረቶች፤ ጀነሬተሮች፤ የእጅ ጋሪዎች፤ በርሜሎችና የውሃ መሳቢያ ቱቦዎች በየጥጉና መስክ ላይ ወድቀው ለበለጠ ለብልሽት ከመዳረጋቸው በተጨማሪ የአካባቢ ብክለት እያስከተሉ መሆኑ፤

የተሽከርካሪዎችን አያያዝ በተመለከተ፣

የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን፤ እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ቁጥር ፩. የመ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝገቡ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜትር ቆጣሪ ጌጁ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ ይኖርበታል በሚለው መሰረት ለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ኢ.ት 4-0169 ሱዙኪ ሞተር ሳይክል የኪ/ሜትር ቆጣሪ ጌጁ የማይሰራ ቢሆንም አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤
- የታርጋ ቁ. ኢ.ት 4-00116 ቶዮታ አውቶሞቢል፣ የታርጋ ቁ. ኢ.ት 4-08163 ኒሳን ፓትሮል፣ የታርጋ ቁ. ኢ.ት 4-18304 ኒሳን ፒክአፕ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

<u>**የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑ፤**</u>

- በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ቁጥር 1 የመንግስት መ/ቤት በግዥ በስጦታ፣ በዝውውር… ወ.ዘ.ተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ መካተት ካለባቸው ውስጥ በፊደል ሰ "የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሊለው አንዱ መሆኑን ቢገለጽም በመ/ቤቱ ዝርዝራቸው ከታች የተገለፁ 3 ተሽከርካሪዎች፣ ኢ.ት 4-18751 ቶዮታ አውቶሞቢል፣ ኢ.ት 4-22426 ቶዮታ ፒካአፕ፣ አንድ ቀይ ቶዮታ ኮሮላ ታርጋ ቁጥር እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላትና አገልግሎት ሳትሰጥ ለብዙ ዓመታት የቆመች መሆኑ፤
- በመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ሶስት ሞተር ሳይክሎች፣ ኢ.ት 4-0169 ሱዙኪ ሞተር ሳይክል፣ ኢ.ት 4-0092 ሞተር ሳይክል፣ ኢ.ት 4-1149 ሞተር ሳይክል፣ ሞተር ሳይክሎቹ በሪከርድና ማህደር ክፍል የሚተዳደሩ በመሆኑ የትራንስፖርት ስምሪት ክፍል እንቅስቃሴያቸውን እና ደህንነታቸውን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፤
- መረጃቸው በትራንስፖርትና ስምሪት የስራ ክፍል ውስጥ የማይገኝና ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ለረጅም ጊዜ መስክ ላይ ቆመው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ ያሉ አአ 4-565 ሞተር ሳይክል፣ አአ ኮድ የሌለው 1398 ሞተር ሳይክል፣ አአ 4-797 ሞተር ሳይክል መሆኑ፤

በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች፤

- በውጭ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፣ ሚሲዮኖች እና የዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች

በትምህርት ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 5,375,664.79 በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ትምህርት ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፡-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የትምህርት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የመ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓለማ፡-

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የመ/ቤቱን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት ፡-

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በትምህርት ሚኒስቴር የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የትምህርት ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኢ.ፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

3. **የወጪ ሂሳብ፤**

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች መ/ቤቱ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙን፣ የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን እንዲሁም ለታቀደው ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1.1.1 **በተሰብሳቢነት መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ፤**

1.1.2 **ግኝት፡-**

የመንግሰት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል ሰኔ 2004 ዓ.ም በወጣው የመንግሰት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- መ/ቤቱ በሃገራችን ባለው የመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮች አሰለጣጠን ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከኮሌጆች ለተውጣጡ 15 ባለሙያዎች የተቋቋመ የጥናት ግብረ ሀይል የመጀመሪያው ዙር ለ20 ቀን በአራራት ሆቴል ጥናቱ ሲካሄድ፤ ከብሪቲሽ ካውንስል ከሚገኘው የሚተካ በሚል ለውሎ አበልና ለሙያ አበል ብር 478,200.00 ክፍያው ከመደበኛ የተፈፀመ ሲሆን በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አላግባብ በቀጥታ ወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

1.1.3 **ስጋት፡-**

- ✓ የመንግስት ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ በተሰብሳቢ መያዝ የነበረበትን ሂሳብ በወጪ ከተመዘገበ ሂሣቡን ለመከታተል ካለማስቻሉ በተጨማሪ ለመደበኛ ስራ የተደለደለው በጀት ለታለመለት ዓላማ ሳይውል ሊቀር ይችላል፡፡

1.1.4 **የማሻሻያ ሀሳብ ፡-**

አላግባብ በወጪ የተዘገበው ሂሣብ በተሰብሳቢነት ተይዞና ክትትል ተደርጎበት ለመደበኛው ሂሳብ ተመላሽ ለሆን ይገባል፡፡

1.1.5 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**

ሂሳቡ ከብሪትሽ ካውንስል ተተክቶአል ለወደፊት እንደዚህ አይነት የሚተካ ሂሳብ ሲያጋጥመን በተሰብሳቢ ይዘን ገንዘቡ ሲገባ ወደ ወጪነት የሚቀየር አሠራር የምንቀበል ይሆናል:: በማለት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

1.2.1 **በመመሪያውና በውሉ መሠረት ያልተቀነሰ (የጉዳት ካሳ)፣**

1.2.2 **ግኝት፡-**

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ላዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙት በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጫት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡- መ/ቤቱ የኤሌክትሮኒክስና የቢሮ ጥገናና ተዛማጅ እቃዎች ግዥ ለመግዛት ባወጣው ግልጽ ጨረታ ኤን ኤም ኤች ትሬድንግ ኀ/የተ/የግል ማህበር በማሸነፍ በብር 636,725.00 በቀን 20/07/2009 ውል የያዘ ሲሆን በውሉ መሰረት እቃዎቹን በ15 ቀን ውስጥ ማለትም እስከ 05/08/2009 እንደሚያስገባ ውል የያዘ ቢሆንም እቃዎቹ ገቢ ያልሆኑበት ምክንያት አሳማኝ ማስረጃ ሳይኖር መግባት ከነበረበት ቀን ከ35 ቀናት በኋላ በ10/09/2009 ገቢ የሆነ በመሆኑ ድርጅቱ ላዘገየበት የጉዳት ካሳ በመመሪያውና በውሉ መሰረት ከጠቅላላ ውል ብር 22,285.06 (636,716.26*1/1000*35) መቀጫት ሲገባው ምንም አይነት የጉዳት ካሳ ባለመቀጣቱ መ/ቤቱ ማግኘት የነበረበትን ብር 22,285.06 የጉዳት ካሳ ገቢ ያሳጣው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.2.3 **ስጋት፡-**

ዕቃው በወቅቱ ባለመቅረቡ በመ/ቤቱ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.2.4 **የማሻሻያ ሀሳብ፡-**

ከውልና ከመመሪያ ውጪ ላዘገየበት ለመ/ቤቱ ገቢ መሆን የነበረበት የጉዳት ካሳ አቅራቢ ድርጅቱ እንዲከፍል ማድረግ አለበት፡፡

1.2.5 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**

- የመጀመሪያ የግዥ ውል ይህንን የጉዳት ካሳ ያላገናዘበና በውልም ያልታሰረ ከመሆኑም በላይ አሁን እንቀጣለን ብንል እንኳን አቅራቢውን ለማግኘት የማንችል መሆኑን እየገለጽን ከግኝቱ በመነሳት አሁን ውሉም የተስተካከለና ሌሎች በዚህ አይነት የዘገዩ አቅራቢዎችን መቀጫት የጀመርን መሆኑን እንገልፃለን:: በማለት ገልፀዋል፡፡

1.3.1 መ/ቤቱ ለፈጸመው ግዢ በወቅቱ ክፍያ ባለመክፍሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት፤

1.3.2 ግኝት፡-

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግገር አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 7 አንቀጽ 29 ቁጥር 29.2 የውል አፈጻጸምን የሚከታተለው የመንግሰት መ/ቤት አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል ይላል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አንቀጽ 29.3 የመንግስት መ/ቤት በውል ስምምነቱ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል፡

ሀ. ተከታታይ ክፍያ በወቅቱ መፈጸም፤

ለ. አቅራቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፤

ሐ. አቅራቢው የውል ግዴታውን መወጣት እንዲችል ህጋዊ የሆነ እገዛ በማድረግ የውል አፈጻጸሙን የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል ይላል፡፡

በዚህ መሰረት የመ/ቤቱ የግዥ ወጪዎች በመመሪያው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡- መ/ቤቱ ለከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን ለመግዛት የሚያማክር የግዥ አማካሪ ለመቅጠር በ25/02/1998 በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በግልጽ ጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈው የግዥ አገልግሎት ድርጅት በቀን 14/01/1999 በብር 2,983,757.20 ለመስራት ውል ተፈራርሞ ስራውን ከጀመረ በኋላ የስራው 50% ክፍያ ተፈፅሞለት በ22/10/2003 ውሉ ተቋረጠ፡፡ ሆኖም ስራው 80% ስለደረሰ ቀሪው 30% ብር 963,577.48 ሊከፈለኝ ይገባል በማለት እንዲከፈለው በተደጋጋሚ በመጠየቁ፤ የመ/ቤቱ ሚኒስትር ዴኤታ በቀን 16/04/2007 በቁጥር 7/260/1349/07 ለድርጅቱ ቀሪውን ብር በጠየቀው መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የታዘዘ ከመሆኑ በተጨማሪ የመስሪያ ቤቱ የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በ22/03/2007 ለሚኒስትሩ ቢሮ ኃላፊ በተጻፈ ማስታወሻ የውሉን 80% ያጠናቀቀ ከሆነ ድርጅቱ የጠየቀው ቀሪ 30% ክፍያ እንዲከፈለው ቢደረግ የተሻለ መሆኑን ምክንያቱም ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ቢሄድ የማያዋጣ እና መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳርግ ከማድረጉ በተጨማሪ ከተቋሙ ጋር ያለውን የመልካም ስራ ግንኙነት እንዳያሻክር ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል አስተያየት የሰጠ ቢሆንም እንዲከፈል በሚኒስቴር ዴኤታው የታዘዘና የህግ አገልግሎትም ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳረግ መከፈል እንዳለበት ቢያሳስብም መ/ቤቱ ክፍያውን ሳይከፍል

በመቅረቱ ድርጅቱ ክስ በመመስረቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 13/01/2009 በዋለው ችሎት ከተቋረጠበት 14/10/2003 ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በጠቅላላው 5 ዓመት ከ7ወር ያልተከፈለውን ብር 963,577.48 እና 9% ህጋዊ ወለድ ብር 484,197.68 በድምር ብር 1,447,775.15 እንዲከፍል በፍርድ ቤቱ በመወሰኑ መ/ቤቱ አላግባብ ለብር 484,197.68 የክትትል እና የአሰራር ችግር ምክንያት መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ተዳርጓል፡፡

1.3.3 ስጋት፣

- ግዥዎችን በውሉ መሰረት አፈጻጸማቸውን ተከታትሎ እንዲፈጸሙ እና በወቅቱ ክፍያ እንዲፈጸም አለማድረግ መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- የመንግስትን ደንብና መመሪያ ተግባራዊ አለማድረግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.3.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለወደፊቱ በመመሪያውና በውሉ መሰረት ግዥዎችን በመፈጸም ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ያለበት ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን ችግር በወቅቱ የተከናወነውን የግዥ ሂደትና ያለበትን ደረጃ ተከታትሎ ክፍያ እንዲፈጸም ባለማድረጉ መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጭ እንዲዳረግ ያደረጉ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ክፍያው የተከፈለው ፍ/ቤት አስገድዶን እንጂ ትክክል ሆኖ አይደለም ምክንያቱም የ1999 የበጀት አመትን በ2009 እንድከፈል መጠየቁ፣ አቅራቢው በወቅቱ ጠይቆ እንዲከፍል ማድረግ ሲገባው አለመጠየቁ የድርጅት /የግዥ አገልግሎት/ ችግር መሆኑ፣ ሌላው ዋና ዶክሜንት ሳይኖር በኮፒ እንድንከፍል መደረጉ ትክክል ያለመሆኑን እንገልፃለን:: በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

1.4.1 ያለጨረታና ያለውድድር የተፈጸመ ግዥ፣

1.4.2 ግኝት፡-

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ፣ እንዲሁም ሰኔ 2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በዚህ መሠረት ለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በግልጽ ጨረታ መፈጸም

የነበረበት በድምሩ የብር 1,778,791.68 ግዥ ያለምንም ውድድር በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

(ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል)

1.4.3 ስጋት፡-

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና የውጤታማነትን ጥቅም ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ ማከናወን ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡
- የመንግስትን ገንዘብ ለምዝበራ ሊያጋልጥ ከማስቻሉ በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.4.4 የማሻሻያ ሀሳብ፡-

- የመንግስትን ገንዘብ አግባብ ካልሆነ ወጪ ለመከላከል እና ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃት እና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ግዥዎች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያው መሠረት መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡
- ለወደፊቱ ከአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ የሚፈጸሙ የተቆራረጡና ተደጋጋሚ ግዥዎች እንዳይከሰቱ የሚመለከተው አካል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ግዥዎችን በዓመታዊ የግዥ እቅድ ውስጥ በማካተት በእቅዱ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1.4.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ለአባ ገዳ አዳራሽ የተከፈለበት ለሁለተኛው ትምህርት ዘርፍ ስትራቴጂ እቅድ ንቅናቄ ለመፍጠር ከሁሉም የኢትዮጵያ ወረዳዎች፣ ከተሞች፣ ክልሎች፣ ከፌዴራል መ/ቤቶች የሚመለከተቸው አመራሮች የተሳተፉበትን ጉባኤ ለማካሄድ በአዳማ ይህንን ተሳታፊ የሚይዝ አዳራሽ ባለመኖሩ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ታምኖበት የተካሄደ መሆኑና እንዲሁም የተሳተፊዎች ቁጥራቸው 1621 በላይ በመሆናቸው፣
- ሌሎች ሆቴሎችም የሀገር አቀፍ ፈተናን የሚከታተል ኮማንድ ፖስት 24 ሰአታትን ስለሚከታተል ቱሪስት ሆቴል ቅርባችን ስለሆነና የፈተና ሚስጥራዊነቱ እንዲጠበቅ ተብሎ ከዚያው ኮማንድ ፖስቱ የተስተናገደበት የመስተንግዶ ሂሳብ በመሆኑ እንዲሁም የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና እንግዶች በበአላት ቀናት ስብሰባ ሲያካሂዱ የተስተናገዱበት ስለሆነና ይህም በግዥ አዋጅ ቁጥር649/2001 አንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ ረ መሠረት የተገዛ ግዥ እንጂ ሆን ተብሎ ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ግዥ ያለመሆኑን እንገልፃለን:: በማለት በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

1.5.1 ማስረጃ ሳይቀርብለት የተፈጸመ ወጪ

1.5.2 ግኝት

በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ለክፍያው ትክክለኛ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፣ ሚሲዮኖችና እና በዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ በትክክል ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምር ብር 157,383,533.13 ክፍያ በመፈጸም በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፡፡

(ዝርዝሩም በአባሪ ቁጥር 2 ተመልክቷል)

1.5.3 ስጋት፡-

- ለተማሪዎች የተላከው ገንዘብ በአግባቡ ላይደርስ ይችላል፡፡
- የተሟላ የክፍያ ሰነድ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያዎችን መፈጸም የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

1.5.4 የማሻሻያ ሀሳብ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት መሟላት የሚገባቸውን ሰነዶች በወቅቱና በአግባቡ ለመቅረባቸው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- ተማሪዎች በትምህርት ላይ መሆናቸውን እና የተላከው ገንዘብ በትክክል መድረሱን የሚረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

1.5.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ስጋቱ ትክክል መሆኑን እየገለጽን ሚኒስትር መ/ቤታችን በ2009 በጀት አመት ለተማሪዎች የተላከ የኪስ ገንዘብ ለተማሪወቹ ስለመድረሱ የመሠራት ሥራ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን እስከ 2008 በጀት አመት ወደ ህንድ ሀገር የተላከውን ገንዘብ በ2009 በጀት አመት ሂሳብ የማጥራት ሥራ ተሰርቷል። በ2010 በጀት አመት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ከፍተኛ ገንዘብ ከተላከላቸው ህንድ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቻይና፣ እና ሩሲያ፣ የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች በመላክ የሚሠራ ይሆናል። ሌሎችም የአሠራር ሥርአት በመዘርጋት ከሚመለከተቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የሚሠራ መሆኑን እንገልፃለን በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

1.6.1 በመ/ቤቱ 11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስለተከፈለ የቅድመ ክፍያ ሂሳብ

1.6.2 ግኝት፡-

በፌዴራል መንግሥት የግዥ መመሪያ ሰኔ 2003 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 16.26 ቁጥር 1 በመንግሰት ግዥ አፈጻጸም እንደ አስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30% /ሰላሳ/ የሚደርስ ቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል ይላል፡፡ ነገር ግን የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታና መሰረተ ልማት እስከ ሰኔ 30/2009 ለኦዲት በቀን 12/12/2009 በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መሰረት የኦዳቡሉቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ለማከናወን ከ11 ህንጻና የግንባታ ስራ ተቋራጮች ጋር በቀን 20/08/2008 እና ከአንድ የመሰረተ ልማት ተቋራጭ ጋር በቀን 05/07/2009 ውል የተያዘ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ የሚውል የቦታ ርክክብ ሳይደረግና ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባበት አካባቢ ላሉ ተነሺዎች የካሳ ግምት ሳይቀርብና ካሳ ሳይከፈላቸው አስቀድሞ ውል ከመያዙ በተጨማሪ የህንጻ የስራ ተቋራጮች የቦታ ርክክብ ሳያደርጉና ወደ ስራ ሳይገቡ ቅድመ ክፍያ ለ9 ኮንትራክተሮች የዋናውን ውል 20% በ2008 በጀት ዓመት በድምር ብር 40,594,366.64 ከአንድ ዓመት በላይ እና ለአንድ ኮንትራክተር በ2009 15% ብር 31,442,798.11 ከሶስት ወር በላይ ምንም ዓይነት ስራ ሳይሰራ የተከፈለ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 በድምር ብር 72,037,164.75 የመንግስት ገንዘብ በህንጻ ግንባታና መሰረተ ልማት ስራ ተቋራጭ ድርጅቶች እየተጠቀሙበት መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

(ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል)

1.6.3 ስጋት፡-

- ተቋራጭ ድርጅቶች ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ ሳይመቻች ቅድመ ክፍያ መክፈል የመንግስትን ገንዘብ ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲሆን ያደርጋል፤
- የተሟላ የተመቻቸ የቦታ ርክክብ ሳይኖር እና ተቋራጮች ስራውን ሳይጀምሩ የቅድሚያ ክፍያ እንዲከፈል ማድረግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.6.4 የማሻሻያ ሀሳብ፡-

ተቋራጭ ድርጅቶቹ ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ ሳይመቻች እና ስራውን ለመጀመር የተመቻቸ ሁኔታ ሳይኖርና ስራ ሳይጀምሩ ቅድሚያ ክፍያ መክፈል የመንግስት ገንዘብ ለግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያስችል አሰራር በመሆኑ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነት ክፍተት እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.6.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በአዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ እንደሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች የካሳው ጉዳይ ይጠናቀቃል በሚል እሳቤ ከተቋራጮች ጋር ውል ተይዞ ቅድሚያ ክፍያ ቢፈጸምም በካሳው ምክንያት መሬቱ ነጻ ሊሆን ባለመቻሉ የግንባታ መርሃ ግብሩ ከዓመት በላይ ዘግይቷል፡፡ በተለይ በ2008 ዓ.ም የካሳ ግምቱን በወቅቱ ለማስተመን የጭሮ ወረዳ አስተዳደር ሥራ ኃላፊዎች በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ ተቀያይረው ስለነበረ በጉዳዩ ላይ የሚመለከተውን አካል እንኳ አግኝቶ ለማነጋገር አልተቻለም ነበር፡፡
- አስተዳደሩ የካሳ ክፍያውን ለማሻሻል ፍላጎት አላሳዩም፡፡ ፍቃደኛም አልነበሩም፡፡ በዚህ የተነሳ ብዙ መጻጻፍ ተደርጎ መግባባት ላይ ባለመደረሱ ለግንባታ የተወሰነውን የመሬት መጠን መቀነስ አማራጭ በማድረግ 100 ሄክታር እንዲሆን ቢወሰንም በርካታ ተነሺዎች መሬቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል ሰበብ የክልሉም መንግሥት ማስገደድ ባለመቻሉ ከስታንዳርዱ በታች 73 ሄክታር ብቻ ለመረከብ ተችሏል፡፡ በሁሉም ሳይቶች ግንባታ እንዲጀመር ውል እንደተያዘ ቅድሚያ ክፍያ ለተቋራጮች ተከፍሏል፡፡

2. የተሠብሣቢ ሂሳብ፣

2.1.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ፣

2.1.2 ግኝት፡-

የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ቁጥር 4/ሀ-ሰ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ላይ፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ብር 67,156,467.64 ከ 1 ዓመት እስከ 15 ዓመት ድረስ የቆየ የተሰብሳቢ ሂሳብ ያለ ሲሆን በተሰብሳቢነት ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ ብር 41,479,809.89 ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ የሚታይ ሲሆን ከማን እንደሚሰበሰብ እና በትክክል የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

	ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት	ከ1 -5 ዓመት	ከ5-10 ዓመት	ከ10 ዓመት በላይ	በጠቅላላው ብር
	-	15,376,657.75	10,300,000.00	41,479,809.89	67,156,467.64

2.1.3 ስጋት፤

- የመንግስትን ገንዘብ በወቅቱ አለመሰብሰብ ለገንዘብ ጥፋትና ብክነት መንስዔ ሊሆን ይችላል፡፡
- በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረድ ቁጥጥር ካልተደረገ ለውዝፍ ሰነድ ክምችት መንስዔ ይሆናል፡፡
- በወቅቱ ተሰብስቦ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ውስን የመንግስት ሀብት /ገንዘብ/ ያለሥራ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡

2.1.4 የማሻሻያ ሃሳብ፤

በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአፋጣኝ እንዲወራረድ፤ ለወደፊቱ የቅድሚያ ክፍያዎች በደንቡና መመሪያው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረዱ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

2.1.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ብር 347,863,256.53 የLC እና ቅድመ ክፍያ ሂሳቦች በተሰብሳቢነት በበጀት አመቱ የተያዙ መሆናቸውን ማስረጃ ለኦዲተሮቹ የሰጠናቸው ሲሆን ቀሪ ማስረጃዎችንም አያይዘን አቅርበናል፡፡

- ብር 840,08፡4.06 ከመደወላቡ ዩኒቨርስቲ ገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሰኔ 1999 Block አድርጎ የወሰዱበት Debit አድቫይስና ደብዳቤ ስላለን የተወራረደ ነው፣
- ብር4,321,176.56 ከደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ገንዘቡን ፈሰስ ለማድረግ ተስማምተናል
- ብር 3,815,641.50 የባህር ሎጂስቲክ ድርጅት ከባንክ ሂሳባችን በሕግ በተሰጠው ሥልጣን ቆርጦ የወሰደና የተወራረደ ነው፤ ቀሪው በ2010 በጀት ዓመት እየተጣራ የሚወራረድ ይሆናል፡፡
- ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ብር 41,479,809.89 በመ/ቤቱ ሰነድ አጣሪ ኮምቴ ተጣርቶ ከሂሳብ መዝገብ እንዲሰረዝ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብበር ሚኒስቴር የተላከና ውጤቱን እየተጠባበቅን ነው፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

2.1.6 የኦዲተሩ አስተያየት

- በምላሹ ላይ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተበት ብር 347,863,256.53 እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም ማስረጃ ቀርቦለት የተረጋገጠው ብር 344,333,827.35 በመሆኑ ለቀሪው ብር 3,529,429.18 ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

- ለመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 840,084.06 እና ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ብር 4,321,176.56 ስለመወራረዱና ፈሰስ ሰለመደረጉ በሰጡት ምላሽ ላይ የተገለፀ ቢሆንም ማስረጃው ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

2.2.1 **በ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ወደ ሪፖርት ያልተላለፈ**

2.2.2 **ግኝት**

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አየያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል ሀ እና ለ ላይ የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሂሳብ ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበትና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው የአጠቃላይ የሂሳብ ሌጀር ሚዛን ወደ ገቢ፣ ወጪ፣ ዝውውር፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ በትክክል መተላለፍ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመመሪያው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በበጀት ዓመቱ በ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ /detailed transaction/ ላይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምር ብር 822,952,048.44 ሲሆን በዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የተደረገ የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምር 666,503,982.29 በመሆኑ የበጀት ዓመቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት በብር 156,448,066.15 (822,952,048.44 - 666,503,982.29 = 156,448,066.15) ዝቅ ብሎ (understate) ሪፖርት የተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

2.2.3 **ስጋት፣**

በትክክለኛው የሂሳብ እንቅስቃሴ የተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ወደ ሂሳብ ሪፖርት አለመተላለፍ የሂሳብ እንቅስቃሴውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉ በተጨማሪ የመ/ቤቱን ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የሃብት መጠን በብር 156,448,066.15 (understate) ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

2.2.4 **የማሻሻያ ሀሳብ**

ወደ ሂሳብ ሪፖርት ያልተላለፈው ተሰብሰቢ ሂሳብ ተጣርቶ ትክክለኛው ምዝገባ እንዲደረግ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

2.2.5 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**

በ11ዱ ዩኒቨርስቲ ግንባታ ኘሮጀክት ጽ/ቤት ከዝርዝር የሂሳብ እንቅስቃሴ ወደ ሪፖርት ያልተላለፈ ብር 156,448,006.15 ዝቅ እንዲል ተደርጓል ለባለው በሂሳብ እንቅስቃሲ መዝገብ ለእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ የሚታየው ተሰብሳቢ ትክክል ሲሆን

ይህ የተፈጠረበት በIFMIS SYSTEM ችግር ነው የሚል ግመት መኖሩን ከኦዲተሮቹ ጋር ተነጋግረናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

2.2.6 **የኦዲተሩ አስተያየት**

ለኦዲት በቀረበው የበጀት ዓመቱ ዝርዝር ምዝገባ /TR/ ያለው የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምርና በበጀት ዓመቱ ሪፖርት በተደረገው መካከል ያለ ልዩነት መሆኑን በግልፅ የሚታይ ሲሆን ከላይ የተሰጠውን ምላሽ ትክክለኛነት የሚያሳይ ምንም ማሰረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

3. **ተከፋይ ሂሳብ፣**

3.1.1 **በወቅቱ ያልተወራረደ የተከፋይ ሂሳብ**

3.1.2 **ግኝት**፡-

የተከፋይ ሂሳቦች በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከሀ-ሠ በተዘረዘረው መሠረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2001 እስከ 2009 በጀት ዓመት ጀምሮ የቆየ በድምሩ ብር 4,724,478.22 እንዲሁም በ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች ብር 4,433,587.47 በጠቅላላው ብር 9,158,065.69 ውዝፍ የተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፡፡

	ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት	ከ1 -5 ዓመት	ከ5-10 ዓመት	ከ10 ዓመት በላይ	ድምር
የሚ/ር መ/ቤቱ	-		4,724,478.22	-	4,724,478.22
የ11 ዩኒቨርሲቲዎች	4,433,587.47	-	-		4,433,587.47
ድምር					9,158,065.69

31.3 **ስጋት፣**

ተከፋይ ሂሳብ (ዕዳ) በበጀት ዓመቱ ሳይከፈል ቀርቶ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት ዞሮ እንዲከፈል መደረጉ ሊከፈል የተቀመጠውን ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ እና መንግስት ባለ ዕዳ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.1.4 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

- የተከፋይ ሂሳቦችን ክምችት ለመቀነስ ሂሳቡ ለባለቤቶች በወቅቱ መከፈል ወይም የማይከፈሉ ከሆነም በተከፋይ ሂሳብ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት በሂሳቡ ላይ በወቅቱ ተገቢው ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

- ለማን እንደሚከፈል የማይታወቀውን ተከፋይ ሂሳብ ጉዳይ በማጣራት ባለቤቱ ካልታወቀ ወደ ሃብትነት እንዲቀየር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3.1.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከብር 962,698.52 ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ከሚከፈል በስተቀር ሌሎቹ አሁን የተከፈሉ ተከፋይ ሂሳቦች ናቸው ይህንን የሚያሳይ ሁለት ገጽ ማስረጃ አያይዘን ልከናል፡፡ በማለት በላኩት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

3.1.6 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

- በተላከው ምላሽ ላይ ካለው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ያልተከፈለው ብር 962,698.52 ሲሆን ሌላው ተወራርዷል የሚል ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም በአጠቃላይ የታይ ከነበረው ብር 7,688,569.23 የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ስለ መወራረዱ ማስረጃ የቀረበለት ለብር 2,964,091.01 ብቻ በመሆኑ ብር 4,724,478.22 አሁንም በተከፋይነት የሚገኝ ስለሆነ ብር 962,698.52 ብቻ በተከፋይነት አለ እንዲሁም ማስረጃውን አያይዘን አቅርበናል የሚለው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

4. <u>የበጀት ሂሣብ፣</u>

4.1.1 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛና የካፒታል በጀት፣</u>

4.1.2 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀጽ 24 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በሚለው ስር ‹‹የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳይረጋገጥ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማድረግ ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል››ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደለት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት የ12 ወር የበጀትና የወጪ አፈጻጸም ንጽጽር ከ10% በላይ በስራ ላይ የዋለውና ያልዋለ በጀት ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደለት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት የ12 ወር የበጀትና የወጪ አፈጻጸም ንጽጽር ከ10% በላይ ሲታይ ከመደበኛ ብር 20,272,459.61 እና ከካፒታል ብር 254,268,290.98 በድምር ብር 274,540,750.59 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፡፡
2. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ከተመደበው የካፒታል በጀት ብር 278,210,628.39 ስራ ላይ ያልዋለ ሲሆን ብር 349,561,836.61 ደግሞ ከበጀት በላይ ጥቅም ላይ ውሎ ተገኝቷል፡፡

(ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 5 ተመልክቷል)፡፡

4.1.3 <u>ስጋት፣</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን በጀት ባለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ ላይደርስ ከመቻሉ በተጨማሪ ሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ሊጠቀሙበት የሚችሉት ውስን የመንግስት ሀብት /በጀት/ ያለጥቅም እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡
- የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በላይ በጀት መጠቀም የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጥሰት የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ውስን የመንግስት ሃብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

4.1.4 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፡-</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ በመጠቀም የመ/ቤቱ ዕቅድና የበጀት ክንውን የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ማናቸውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ የተፈቀደ፣ በዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ የተስተካከለ በቂ በጀት መኖሩ ሳይረጋገጥ ማንኛውንም ክፍያ መፈጸም እንደሌለበትና ለወደፊቱ ችግሩ እንዳይፈጠር የሚመለከተው አካል ቁጥጥር ሊያደረግበት ይገባል፡፡

4.1.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ብር 200,969,820.00 በአጠቃላይ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮጀክት ሁለት ላይ ለመጽሀፍት ህትመት የተያዘ በጀት ሲሆን ከብድርና ተራድኦ የፋይናንስ ምንጭ የበጀት እጥረት ሲያጋጥም ብቻ በመንግስት የተመደበ በጀት ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ከብድርና ተራድኦ የፋይናንስ ምንጭ ለተያዙ ተግባራት እጥረት ባለመፈጠሩ ጥቅም ላይ ሳይውል ቢቀርም በውላችን መሰረት የበጀት እጥረት ባጋጠመን ጊዜ መጠቀም የምንችል መሆኑ፡
- በ11 ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደልን በጀት ውስጥ 84.19% ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ከበጀት ዓመቱ ከተፈቀደ በጀት ስራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት፡-
  - የግንባታ ሂሳብን በተመለከተ ለሰኔ ወር 2009 የተጠየቀው የጥሬ ገንዘብ ጥያቄ በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ሙሉ በሙሉ ባለመለቀቁና የስራ ተቋራጮች የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ስራ ላይ ሳይውል የቀረ መሆኑ፡
  - የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች እቃዎች ግዥ ለመፈጸም በወጪ መደብ 6313 እና 6314 የተፈቀደ በጀት ስራ ላይ ሳይውል የቀረው የግዥ ሂደቱ በመጓተቱ፣ የውጪ ግዥ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ለመክፈት ባለመቻሉ እና የሃገር ውስጥ ግዥም

ቢሆን የቅድሚያ ክፍያ ሆነ ሊቀርብ ለሚችለው እቃ ክፍያ መፈፀም ባለመቻሉ ነው፡፡

- በ6255 ለጭነት ተፈቅዶ ስራ ላይ ያልዋለ በጀት የህንጻና የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች በመራሃ ግብሩ መሰረት ባለመከናወኑ የስሚንቶ ስርጭት በታቀደው መሰረት በታቀደው መሰረት ባለመከናወኑ ምክንያት ስራ ላይ ያልዋለ ነው፡፡
- በ6316 የሂሳብ መደብ የተመደበው የሂሳብ መደብ ለኮንትራት አስተዳደርና ለሱፐርቪዥን ስራ የተመደበ ሲሆን አማካሪ ድርጅቶች በወቅቱ የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረባቸው መሆኑ፣
- በ6322 እና 6323 የሂሳብ መደብ ከበጀት በላይ ስራላይ ውሏል ለተባለው ብር 349,561,836.61 ከበጀት በላይ ስራላይ የዋለ በጀት ሳይሆን በ2008 በጀት ዓመት የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ተሰብሳቢ በመደረጉ እና 5% የመያዣ ሂሳብ የIFMIS ሲስተሙ በወጪነት ስለመዘገበው እና የዘንድሮን በጀት በወጪነት በመንካቱ የመጣ ልዩነት ነው፡፡ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

4.1.6 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

- በ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፡-
  - ብር 349,561,836.61 ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ በጀት ሳይሆን በ2008 በጀት ዓመት የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ተሰብሳቢ በመደረጉ እና 5% የመያዣ ሂሳብ የIFMIS ሲስተሙ በወጪነት ስለመዘገበው እና የዘንድሮን በጀት በወጪነት በመንካቱ የመጣ ልዩነት ነው በሚል የተሰጠው ምላሽ የአመዘጋገብ ችግር በመሆኑ እና የ2009 በጀት የነካ በመሆኑ እና ለዚህም ማስተካከያ ሳይሰራለት የሂሳብ ሪፖርቱን የነካው በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

5. <u>ንብረት፣</u>

5.1.1 <u>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች፣</u>

5.1.2 <u>ግኝት፡-</u>

የመ/ቤቱ የንብረት አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አስተዳደር በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001፣ በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአላቂ እቃዎች መጋዘን ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የፕሪንተር ቀለሞች፣ እስኬር ወረቀት፣ መጠረዣ /ሪንግ/ ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመት በላይ መቀመጣቸው፣

- የፍሬንና የሞተር ዘይት ከአላቂ ዕቃዎች ጋር በአንድ ክፍል ተቀላቅሎ መገኘቱ;
- በቁጥር የማይታወቅ በጣም ብዛት ያላቸው ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶኮፒ ማሽኖች፣ ፋይል ካቢኔቶች፣ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ የተሽከርካሪ ጎማዎች እና ሌሎችም ቋሚ እቃዎች በተለያዩ ክፍሎች ታሽገው የተቀመጡ በመሆኑ ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፡
- የተሰባበሩ የሽንትቤት እቃዎች፣ የተለያዩ ብረቶች፣ ጀነሬተሮች፣ የእጅ ጋሪዎች፣ በርሜሎችና የውሃ መሳቢያ ቱቦዎች በየጥጉና መስክ ላይ ወድቀው ለበለጠ ለብልሽት ከመዳረጋቸው በተጨማሪ የአካባቢ ብክለት እያስከተሉ መሆኑ፣

5.1.3 ስጋት፣

- ያለአገልግሎት እቃዎችን በንብረት ክፍል ማስቀመጥ ለብልሽት ከመዳረጉም በተጨማሪ አገልግሎት ላይ የማይውል የሃብት ክምችትን ሊፈጥር ይችላል፡፡
- በወቅቱ መወገድ ያለባቸው ንብረቶችን አለማስወገድ ለበለጠ ብልሽት ሊዳርግ ከመቻሉ በተጨማሪ አካባቢያዊ ብክለት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡
- የሚወገዱ ንብረቶችን ከማይወገዱ ንብረቶች ጋር ቀላቅሎ ማስቀመጥ ማገልገል የሚችሉትን ለብልሽት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- የመንግስት ንብረት አስተዳደር፣ አጠቃቀምና አያያዝ በመመሪያው መሰረት አለማከናወን ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

5.1.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረት ከጥፋትና ከብክነት ለመከላከል ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመቅረፍ የአሰራር ስርዓቱን በአስቸኳይ ማስተካከል ይኖርበታል፡፡

5.1.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ቀደም ሲል የተገዛና በብዛት ተጠቃሚ ስለሌለው እንዲወገዱ ተጠይቆ ውሳኔ የሚጠብቅ ስለሆነ የተቀመጠ፣
- የፍሬንና የሞተር ዘይቶቹ በግማሽና በአንድ ሊትር የተገዙና ይህንንም የሚጠቀሙት ሾፌሮችና ሞተረኞች ስለሆኑና ዘይቱም አላቂ ስለሆነ በአላቂ እቃ ግምጃ ቤት የተቀመጠው፣

- ኮምፒውተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ሌሎችም ኤለክትሮኒክስ ዕቃዎች በሙሉ ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለማስረከብ በደብዳቤ አሳውቀናቸው የሚረከቡት በቀጠሮ ስለሆነ የቀጠሮ ቀን እየጠበቅን በመሆኑ፣

- ጠረጴዛና ወንበሮች ፤ፋይል ካቢኔት እና ሌሎች ቋሚ እቃዎች በ16/12/09 በቁጥር መስ/2ኛ/ደ460/135/09 በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቀው ሲሆን የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ 35፤ጠረጴዛ 5፤ወንበር 20፤አሮጌ ምንጣፍ 10፤ፋይል ካቢኔት 12፤የማስታወቂያ ሰሌዳ 6፤ሼልፍ ባለ እንጨት 1 ድሮር 1 በ18/12/2009 ዓ.ም በሞዴል 19 በሞዴል ቁጥር 382841 ለትምህርት ቤቱ ገቢ ሆኗል

- በትምህርት ሚኒስቴር ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘው ኮድ ኢትዮጵያ በ18/12/09 በተጻፈ ማስታወሻ ጠይቀው 5 የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ በ22/12/2009 ዓ.ም በሞዴል 22 በሞዴል ቁጥር 0297790 ወጪ ሆኖ ተሰጥቷል፣

- ጎማዎች ፣የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ የእጅ ጋሪዎች በተመለከተ፡- የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የሚወገዱ ንብረቶችን እንድናሳውቀው በ1/12/2009 ዓ.ም በቁጥር ግንማ/ሰሀ/ማሰ/44/057 በተጻፈ ደብዳቤ በጠየቀው መሠረት ንብረቶቹ ካሉበት ቦታ በአንድ ላይ በማሰባሰብ 2 መኪና 127 የተለያዩ የተሽከርካሪ ጎማዎች 49 የመኪና ባትሪ 120 የቶነር እቃዎች ቁጥራቸው የማይታወቅ ብረታ ብረቶች 2 የእጅ ጋሪዎች በጥያቄው መሠረት ለማስረከብ በ22/12/09 በቁጥር 27/1-18287/3697/35 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ተሰጥቶ የሚረከቡበትን ቀን በመጠባበቅ ላይ ያለን በመሆኑ፣

- የተሰባበሩ የሽንት ቤት እቃዎች፣ ጄኔሬተሮች እና በርሜሎችን ለማስወገድ የኃላፊዎችን ውሳኔ የሚጠይቅ በመሆኑ ውሳኔ እስከሚሰጥ የሚጠብቅ ስለሆነ፤

- የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን በተመለከተ በትምህርቱ ዘርፍ ድጋፍ የሚሰጡ የተለያዩ ድርጅቶች የሥራ ጊዜአቸውን ጨርሰው ሲሄዱ የተበላሹትን ኮምፒውተር፣ፕሪንተር፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን ለመ/ቤቱ ትተው በመሄዳቸው ምክንያት በመመሪያ መሠረት ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለማስረከብ የተሰበሰቡ ናቸው።

6. <u>የተሽከርካሪዎችን አያያዝ በተመለከተ፣</u>

6.1.1 <u>ግኝት፣</u>

የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን፤ እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9

ቁጥር ፩. የመ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜትር ቆጣሪ ጌጁ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ ይኖርበታል በሚለው መሰረት ለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ኢት 4-0169 ሱዙኪ ሞተር ሳይክል የኪ/ሜትር ቆጣሪ ጌጁ የማይሰራ ቢሆንም አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤
- የታርጋ ቁ. ኢት 4-00116 ቶዮታ አውቶሞቢል፤ የታርጋ ቁ. ኢት 4-08163 ኒሳን ፓትሮል፤ የታርጋ ቁ. ኢት 4-18304 ኒሳን ፒክአፕ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

6.2.1 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑ፤</u>

<u>ግኝት</u>

- በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ቁጥር 1 የመንግስት መ/ቤት በግዥ በስጦታ፤ በዝውውር… ወ.ዘ.ተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ መካተት ካለባቸው ውስጥ በፊደል ሰ "የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌለው አንዱ መሆኑን ቢገለጽም በመ/ቤቱ ዝርዝራቸው ከታች የተገለፁ 3 ተሽከርካሪዎች፤ ኢት 4-18751 ቶዮታ አውቶሞቢል፤ ኢት 4-22426 ቶዮታ ፒካአፕ፤ አንድ ቀይ ቶዮታ ኮሮላ ታርጋ ቁጥር እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላትና አገልግሎት ሳትሰጥ ለብዙ ዓመታት የቆመች መሆኑ፤
- በመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ሶስት ሞተር ሳይክሎች፤ ኢት 4-0169 ሱዙኪ ሞተር ሳይክል፤ ኢት 4-0092 ሞተር ሳይክል፤ ኢት 4-1149 ሞተር ሳይክል፤ ሞተር ሳይክሎቹ በሪከርድና ማህደር ክፍል የሚተዳደሩ በመሆኑ የትራንስፖርት ስምሪት ክፍል እንቅስቃሴያቸውን እና ደህንነታቸውን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፤
- መረጃቸው በትረንስፖርትና ስምሪት የስራ ክፍል ውስጥ የማይገኝና ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ለረጅም ጊዜ መስክ ላይ ቆመው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ ያሉ አአ 4-565 ሞተር ሳይክል፤ አአ ኮድ የሌለው 1398 ሞተር ሳይክል፤ አአ 4-797 ሞተር ሳይክል መሆኑ፤
- በፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ46 ቁጥር 2 በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመሰርቷል የሚባለው በሁለቱ ተዋዋያ ወገኖች ሰምምነት የተደረሰባቸውን

ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የውል ሠነድ ሲፈረም ይሆናል ይላል፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ለጥገና ወደ ጋራጅ ሲገቡ ውል የማይያያዝ በመሆኑ እና መቼ እንደሚወጡ የጊዜ ገደብ በውል ስሌለ ተሽከርካሪዎች ለብዙ ጊዜ በጋራዥ ውስጥ ቢዘገዩ ወይም በጋራዥ ውስጥ በተሽከርካሪዎች ላይ ችግር ቢፈጠር በውል ያልተያዘ በመሆኑ በወቅቱ እንዳይጠገኑ ከማድረጉ በተጨማሪ በህግ ለመጠየቅ የማይቻል መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

6.2.2 ስጋት፣

- ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች የአሽከርካሪዎችን ደህንነት ችግር ላይ ሊጥል ከመቻሉ በተጨማሪ የገንዘብ ብክነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

- አገልግሎት የማይሰጡና የቆሙ ተሽከርካሪዎች በወቅቱ አለመወገዳቸው ለበለጠ ብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

- የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር አለመኖር ንብረቱ የመ/ቤቱ ለመሆኑ ማረጋገጥ ላያስችል ይችላል፡፡

- በትራንስፖርትና ስምሪት የስራ ክፍል ውስጥ የማይታወቁ እና ክትትልና ቁጥጥር የማይደረጉ ተሽከርካሪዎች ለበለጠ ብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ

- መ/ቤቱ ውል ሳይዝ መኪኖችን ለጥጋና ማስገባት በወቅቱ ተጠግነው እንዳይወጡ ምክንያት ከመሆኑ በተጨማሪ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

6.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

- መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ቋሚ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር /ሊብሬ/ የሌላቸውን እንዲያገኙ ማድረግ፣ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ካልተጠገኑ አገልግሎቱን እንዲያቆሙ በማድረግ፣ ሁሉንም ተሽከርካሪዎች የትራንስፖረትና ስምሪት የስራ ክፍል እንዲያስተዳድርቸው ማድረግ፣ የትራንስፖርትና ስምሪት የስራ ክፍል ውስጥ መረጃቸው የማይገኙ ሞተር ሳይክሎች ሙሉ መረጃቸውን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት እና
- ተሽከርካሪዎቹ ለጥገና ወደ ጋረዥ ሲገቡ ውል በመያዝ በዉሉ መሰረት በወቅቱ ተጠግነው እንዲወጡ የሚመለከተው አካል አፋጣኝ መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል፡፡

6.2.3 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የሰሌዳ ቁጥር 4-0169 ሞተር ሳይክል ከአገልግሎቱ አኳያ ያረጀ ሞተር ሳይክል ስለሆነ በካምፓኒው ውስጥ ለጥገና ሲላክ የኪሎ ሜትር ጌጅ የሌለው መሆኑ ያሳወቅን ቢሆንም ያልተቀየረ መሆኑ፣

- በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች በተመለከተ የማስወገድ ስልጣን ለተሰጠው ለንብረት አስወጋጅ መስሪያ ቤት ያሳወቅን መሆኑ፤
- 4-18751ኢ.ት ይህ ተሽከርካሪ ጊዜያዊ ሊብሬ ያለው መሆኑንና በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፡
- 4-22426 ኢ.ት ይህ ተሽከርካሪ ዶክሜንቱ ያልተሟላ ስለሆነ ይህ የእኛ ችግር ስላልሆነ ገንዘብና ኢኮኖሚ ዶክሜንቱን ሲያሟላ የሚወጣ መሆኑ፤
- የመስሪያ ቤቱ ሞተር ሳይክሎች በተመለከተ በወር በአቢሲኒያ ካርድ የሚሞላላቸው ሲሆን የስምሪት አገልግሎቱን በተመለከተ የሰው ሀብት ለፖስታ መልዕክት አገልግሎት በክፍሉ ክትትልና ስምሪት የሚደረግ በመሆኑ ነው ለወደፊቱ ከመዝገብ ቤት ሀላፊ ጋር በመነጋገር መፍትሄ የሚሰጥ መሆኑ፤
- በስምሪት መረጃቸው የሌሉ ሞተር ሳይክሎችን በተመለከተ ለማስወገድ ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ በደብዳቤ ሪፖርት መደረጉን፤
- የውል ስምምነት ወደ ጋራዥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በተመለከተ ከዚህ በፊት በተመረጡ 3 ካምፓኒዎች በቀጥታ የጥገና ስምምነት ተሽከርካሪዎች ለጥገና የሚገቡ ሲሆን መንግስት በነሀሴ 01 /2009/ ዓ.ም ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት መኪና ጥገና ጨረታ እንዲወጣ ለግዥና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ደብዳቤ ተጽፎ በውልና በጨረታ ለማድረግ ስርአት መዘርጋቱን ገልፀዋል፡፡

7. ልዩ ልዩ፤

7.1.1 የውስጥ ኦዲት፤

7.1.2 ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በመ/ቤቱ የተቋቋመው የውስጥ ኦዲት ስርዓት ተገቢ እና በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል ያለው መሆኑን፣ የውስጥ ኦዲትን በነፃነት፣ ውጤታማ፣ ፈጣንና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ መከናወኑን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

- በዚህ መሠረት የመ/ቤቱ በስራ ክፍሉ መዋቅር 9 የሰው ሃይል እንደሚያስፈልገው የተገለጸ ቢሆንም አሁን የስራ ክፍሉ 5 የሰው ሃይል ብቻ ያለው መሆኑ እና ቀሪው 4 የስራ መደብ ያልተሸፈነ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የክዋኔ ኦዲት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይሰራ መሆኑ፡፡

7.1.3 ስጋት፡

- የውስጥ ኦዲቱ ጠንካራና ውጤታማ ላይሆን ይችላል፡፡

- ጥራት ያለው ሪፖርት ላይወጣ ይችላል፡፡
- የመ/ቤቱ የውስጥ ቁጥጥሩ የላላ ሊያደርገው ይችላል፡፡

7.1.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

- የሥራ ክፍሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሰው ኃይሉ እንዲሟላ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- የስራ ክፍሉ የክዋኔ ኦዲት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል

7.1.5 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ለግኝቱ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

7.2 <u>ከእቅድ ውጪ ስለተከናወነ ግዢ</u>

7.2.1 <u>ግኝት፡-</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 22/2 በመንግስት መ/ቤቶች የተዘጋጀው የግዥ እቅድ በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ጸድቆ ለሚመለከታቸው የመስሪያ ቤቱ የስራ ክፍሎች እና ለፌደራል ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በየአመቱ እስከ ሃምሌ 30 መላክ ይኖርበታል ይላል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 33/2 በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ሰኔ 2002 የወጣ የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 5/3 የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የግዥ ስራን እንዲፈጽም የሚደራጀው የስራ ክፍል ስራውን በቡድን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ስልጣን ያለውና ግልጽ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው ይላል፡፡ በዚህም መሰረት መ/ቤቱ የግዥ እቅድና የእቅድ አፈጻጸም በመመሪያው መሰረት የታቀደና የተፈጸመ መሆኑንና ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ውስጥ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሚኒስትር ሾፌሮችና አጃቢዎች የደንብ ልብስ ግዥ ብር 174,600.00 ብቻ ፤ በቀጥታ ግዥ የቴሌቪዥን ድራማ ዝግጅት ብር 5,000,000.00 እና ከባለፈ ዓመት የዞረ የስነ ዜጋና የስነ ምግባር ትምህርት በተማሪዎች ያመጣው የባህሪ ለውጥ ጥናት ግዥ ብር 3,300,000.00 በድምር ብር 8,300,000.00 እና በውስን ጨረታ ብር 450,000.00 ሲሆን ከዚህ ውጭ ሌሎች ግዥዎች በግልጽ ጨረታ እንደሚከናወኑ በእቅዱ የተያዘ ቢሆንም በእቅዱ ከተያዙት ግዥዎች ውጭ፡-

1. የተለያዩ እቃዎች እና የአገልግሎት ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በድምር ብር 8,968,872.88

2. ለተለያዩ እቃዎች እና የአገልግሎት ግዥዎችን በቀጥታ ግዥ በማከናወን በድምር ብር 15,418,733..91

በአጠቃላይ ከመ/ቤቱ እቅድና መመሪያ ወጭ በድምር ብር 24,387,606.79 ከእቅድ ውጪ ግዥ አከናውኖ መገኘቱ፡፡

7.2.2 ስጋት፣

- በመ/ቤቱ ግዥዎችን በእቅድ መሰረት የማይከናወን ከሆነ ውስን የመንግስት ሃብት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ጥቅም ማስገኘቱን ማረጋገጥ አያስቻልም፡፡
- ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ ማከናወን ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ያደርጋል፣ የመንግስትን ገንዘብ ለምዝበራ ሊያጋልጥ ከማስቻሉም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

7.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፡-

- የመንግስትን ገንዘብ አግባብ ካልሆነ ወጪ ለመከላከል እና ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃት እና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ግዥዎች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያው መሠረት መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡
- ለወደፊቱ ከአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ የሚፈጸሙ የተቆራረጡና ተደጋጋሚ ግዥዎች እንዳይከሰቱ የሚመለከተው አካል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ግዥዎችን በዓመታዊ የግዥ እቅድ በማካተት በእቅዱ መሰረት መፈጸም አለበት፡፡

7.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ ተወዳዳሪ ሳይገኝለት ተንጠባጥቦ የቀሩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በዚህ የግዥ ዘዴ እንዲፈጸሙ የተደረጉ መኖሩና ሳይታቀዱ አገልግሎቶቹና እቃዎቹ በበላይ አመራር ለመ/ቤቱ ጠቀሜታው ታምኖበት እንዲገዛ የተፈቀዱ ግዥዎች ያሉ መሆኑ፣ እንዲሁም በማዕቀፍ ግዥዎች እንዲፈጸሙ ታቅዶ ድርጅቶቹ በጊዜ ሳያቀርቡ በመቅረት በስራዎቻችን ላይ እንቅፋት በመፈጠራቸው በልዩ ፍቃድ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ እንዲፈጽሙ የተደረጉ ግዥዎች በመሆናቸው፣
- አንዳንድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ከግዥ ዕቅድ ውጭ የተከናወኑ ግዥዎች ሲሆኑ እነርሱም የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ግዥ ሲሆን ተሽከርካሪዎቹ ብልሽት ሲያጋጥማቸው ብቻ ከአስመጪው ድርጅት የሚጠገኑ መሆኑንና አስቸኳይና ወሳኝ የበላይ አመራር ስብሰባ /ዎርክሾፕ ለጸጥታ እና ሌሎች ጉዳዮች በባህሪያቸው የተወሰነ ቦታ የሚፈልጉ በመሆናቸው በበላይ አመራር በቀጥታ በልዩ ትእዛዝ እንዲፈጸሙ የተደረጉ ግዥ መሆኑ፣

- በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ልዩ ፈቃድ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የህትመት አገልግሎት ግዥ እንዲፈጸሙ የተደረጉ ያሉ መሆኑ፤ የቴሌቪዥን እስፖርት አገልግሎት ግዥ በቀጥታ በኢ.ብ.ኮ (EBC)የተፈጸሙ ያሉ መሆኑ፤ የእስፖንሰር ሺፕ ክፍያ በቀጥታ የተደረጉ መሆኑ እና የማስታወቂያ አገልግሎት ግዥ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የተፈጸሙ መሆኑን ገልፀዋል፤

7.3 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስተዳደር፣

7.3.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 7/4 ላይ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ስለመስሪያ ቤቱ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ፤ ለመመዝገብ፤ ለማከናወን፤ ለማጠቃለል እና ሪፖርት ለማድረግ እንዲያስችላቸው በኮምፒውተር በታገዘ የመረጃ ስርዓት ላይ ተስማሚ ቁጥጥሮችን መዘርጋትና መጠበቅ አለባቸው ይላል፡፡ በዚህ መሰረት የመ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አደረጃጀትና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ኦዲት ሲደረግ፡-

1. **በሚኒስቴር መ/ቤቱ**
   - የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስተዳደር ስትራቴጂካል እና ስትሪንግ ኮሚቴ የሌለ መሆኑ፤
   - የአምስት አመት ስትራቴጅክ እቅድ የሌለ መሆኑ፤
   - ህጋዊ የሆነ እና የጸደቀ የሴኩሪቴ/ የሚስጥር አስተዳደር የሌለ መሆኑ፤
   - የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቀጣይነት እና የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ /disaster recovery plan/ የሌለ መሆኑ፤
   - የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቀጣይነት እና መልሶ ለማቋቋም ከመስሪያ ቤቱ ዉጪ/off-site/ መረጃ ማስቀመጫ የሌለው መሆኑ፤
   - በሰነድ የጸደቀ የተጠቃሚዎች አስተዳደር መስፈርት እና የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

2. **በኢትዮጵያ ትምህርት ምርምር ኔትወርክ**
   - በመረጃ ማዕከሉ /ዳታ ሴንተር/ የሙቀት መቆጣጠሪያ ፋን ሙቀቱን ሙሉ በሙሉ ሊቆቋም ባለመቻሉ በክፍሉ ከፍተኛ ሙቀት እየፈጠረ መሆኑ፤
   - የተጠናከረ የተቀናጀ ተተኪ (የባካብ) ስርዓት የሌለ መሆኑ፤
   - ከመስሪያ ቤቱ ውጭ የመረጃ ማስቀመጫ ማዕከል (off-site Data centre) የሌለ መሆኑ፤

- ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአንድ የመረጃ ማዕከል ብቻ የተሳሰሩ በመሆኑ የመረጃ ስርዓቱ ቢቋረጥ ሌላ የመገናኛ አማራጭ ባለመኖሩ መገናኘትና መረጃ መለዋወጥ የማይቻል መሆኑ፤

3. **በትምህርት ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጅ ማዕከል**

- በቴሌቪዥን መቅረጫ ስቱዲዮ መሳሪያዎች የቆዩና በአናሎግ ስርዓት አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው በዲጅታል ስርዓት ለማከናወን አስቸጋሪ መሆኑ፤

- በቴሌቪዥን መቅረጫ ስቱዲዮ መብራቱ ከዘመኑ ቴክኖሎጅ ጋር የማይሄድ በመሆኑ እና በጣሪያው የዝናብና የመኪና ድምጽ የሚያሰማ በመሆኑ በቴሌቪዥን ስርጭት የጥራት ችግር የሚፈጥር መሆኑ፤

- በአዲስም ሆነ በነባሩ ህንጻ ጣሪያው እያፈሰሰ በመሆኑ በክፍሉ የሚገኙት እቃዎች ለብልሽት የተዳረጉ ከመሆናቸው በተጨማሪ ከፍተኛ ሽታ በመፍጠር ለሰራተኞች የጤና ችግር ከመፍጠሩም በተጨማሪ የአካባቢ ብክለትን የሚያስከትል መሆኑ

7.3.2 **ስጋት፤**

- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የአስተዳደርና የአሰራር ስርዓት እና አደረጃጀት ያልተሟላ መሆኑ በመ/ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የአስተዳደር የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ያልተሟላ መሆኑ በመ/ቤቱ እና በትምህርት ተቋማት መካከል ያለው የመረጃ ልውውጥ እና የስርጭት ስርዓቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡
- በቴሌቪዥን መቅረጫ ስቲዲዮ መብራቱ ከዘመኑ ቴክኖሎጅ ጋር የማይሄድ በመሆኑ የትምህርት ስርጭቱ ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር ያለው ተጠቃሚነት ሊቀንስ ከመቻሉ በተጨማሪ የስርጭት ጥራት ሊቀንስ ይችላል፡፡

7.3.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

- መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስተዳደር አገልግሎትን የተሟላ ለማድረግ ከላይ በተዘረዘሩት ክፍተቶች ላይ ትኩረት በመስጠት፤ የመረጃ ስርዓቱ ደረጃውን የተጠበቀ እንዲሆንና የተሻለ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አካባቢና አስተዳደር በመፍጠር፤ እና
- የመረጃ አጠባበቅ፤የስርጭት ጥራት እና የመረጃ ግንኙነት የተሟላ ለማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን ክፍተቶች ትኩረት በመስጠት የመ/ቤቱ የመረጃ ስርዓት ምስጢራዊ፤ ጥራት ያለው፤ አማራጭ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖርና የተሻለ የኢንፎርሜሽን

ቴክኖሎጂ አካባቢና አስተዳደር በመፍጠር ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር እንዲራመድ የሚያስችለውን የአሰራርና የአደራጃጀት ስርዓት መፍጠር ይኖርበታል፡፡

7.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በመ/ቤቱ የትምህርት ስራ አመራር መረጃ አቅርቦት እና አይሲቲ ዳይሬክቶሬት በዋነኛነት የስራ ክፍሉ በአገር ውስጥ ከሚገኙ ሁሉም የትምህርት ተቋማት የትምህርት መረጃ በማሰባሰብ አመታዊ መጽሔት አዘጋጅቶ በሶፍት ኮፒና በህትመት ማሰራጨትና በግቢውስጥ የሚገኙ ኮምፒውተሮች ሲበላሽ መጠገን ስለሆነ ይህ ክፍል የተቋቀመበትና መጠይቁ የሚጠይቀውን ለማጣጣም መሞከር ተገቢ ይመስለኛል፡፡
- በኢትዮጵያ ትምህርት ምርምር ኔትወርክ የሙቀት መጠኑን የሚቆጣጠር ማሽን በወቅቱ የተወሰነ ሲስተሙ ብልሽት ገጥሞት ስለነበር አሁን ተሻሽሎ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤ ዳታ ማእከሉ ውስጥ ለሚቀመጡ ዳታዎች የባክ አፕ በግዥ ሂደት ላይ ነው፤ ለኢተርኔት አሁን ካለበት ሳይት በተጨማሪ የመረጃ ማዕከል በአይቲ ፓርክ ለመገንባት በሂደት ላይ ሲሆን ለዳታ ማእከሉ የመልሶ ማቋቋሚያ ሳይት ስለሌለው ባለው ዳታ ማእከል የሆነ ነገር ቢያጋጥም ለከ/ት/ት ተቋማት አገልግሎት መስጠት እንደማይቻል ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ሁሉም የተሰጡ አስተያየቶች ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን ነገር ግን መፍትሔ ለመስጠት ጊዜና ሃብት ስለሚጠይቅ ኮስት ኢፌክቲቭ በሆነ መንገድ በእቅድ ተይዞ እየተሰራ እንደሆነ እንገልጻለን፡፡
- የትምህርት ኢንፎርሜሽን ኮምኒኬሽን ቴክኖሎጅ ማዕከል የቴሌቪዥን መቅረጫ ስቱዲዮ መሳሪያዎች አናሎግ የሆኑና የቆዩ በመሆናቸው በዲጅታል እንዲቀየር በ2009 በጀት ቢያዝም ለካሜራ የተወዳደረው ተጫራች አንድ ብቻ በመሆኑና መስፈርቱን ባለማሟላቱ ውድቅ የተደረገ ሲሆን በ2010 በጀት ዓመት ለመግዛት በጀት ተይዞ በእቅድ ተካቷል፡፡ ጥያቄውም ለግዥ አገልግሎት ዳይሬክተር ቀርቦ ለግዥ ኤጀንሲ አሳውቀናል፡፡ የስቲዲዮ መብራቶችን በተመለከተ እስከአሁን ከምህንድስና ቡድን በጹሑፍም ሆነ በቃል የቀረበ ነገር ባይኖርም ሁኔታውን አይተን በቀጣይ የሚገዛበትን ሁኔታ እንዲመቻች በእቅድ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ አሮጌው ሆነ አዲሱ ህንጻ መታደስ እንዳለበት በእቅድ ተይዞ የማዕከሉ የግዥ ውክልና ከግዥ አገልግሎት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዲታደስ አቅርበናል፡፡ ነገርግን የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሙያዊ እገዛ ለማድረግ ባለመቻላቸው አልተሰራም፡፡ ለዚህም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በደብዳቤ ቁጥር ኢኮቴ /2041/101/2009 በቀን 27/11/2009 እንዲሁም በቁጥር ኢኮቴ /5/101/2010 በቀን 2/01/2010 ያሳወቅን ሲሆን በዚህ ዓመት ለማሰራት በጀት በመያዝ በእቅድ ውስጥ ተካቷል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

7.3.5 **የኦዲተሩ አስተያየት**

በመ/ቤቱ የትምህርት ስራ አመራር መረጃ አቅርቦት እና አይሲቲ ዳይሬክቶሬት በኩል የተሰጠው ምላሽ መጠይቁ የመ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ተክኖሎጅ አደረጃጀት አጠቃቀምና አስተዳደር እንዲጠናከር የሚጋብዝ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ትክክል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

7.4 የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር

7.4.1 ግኝት፣

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡

- ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የኮንትራት ሠራተኞች በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ሳይመደቡ ወይም ዘላቂነት ከሌለው የሥራ መደብ ላይ ሳይሰናበቱ እና በመ/ቤቱ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ሳያስፈቅድ በ2009 የሰው ሃብት አስተዳደር ለኦዲት በሰጠው የኮንትራት ሰራተኞች ዝርዝር መግለጫ መሰረት ለ5 ሰራተኞች ብር 214,116.00 ከመመሪያ ውጭ ለኮንትራት ቅጥሮች ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፡፡

ተ.ቁ	የሰራተኛው ስም	የወር ደመወዝ	የ12 ደመወዝ	የሚሰራበት የስራ	የስራ መደቡ መጠሪያ	የተቀጠሩበት ቀን/ወር/ዓ.ም
1	ወ/ሪት መስከረም እሸቱ	2,197.00	26,364.00	ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት	ዳታ ኢንኮደር	7/10/2005
2	አቶ ትንሳኤ ብርሃኑ	2,197.00	26,364.00	//	//	07/10/2005
3	አቶ ሰለሞን ጎሹ	4,867.00	58,404.00	ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት	ከፍተኛ የክፍያ ባለሙያ	15/04/2006
4	አቶ ግርማ ተሰማ	5,304.00	63,648.00	የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት	የሪከርድና ማህደር አስተባባሪ	01/03/2008
5	አቶ ፈቃደ ተሰማ	3,278.00	39,336.00	ኮምኒኬሽን ጉዳዮች	የመስተ አስተባበሪ	01/12/2001

7.4.2 ስጋት፣

- ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም የመንግስት ገንዘብ ብክነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ከመመሪያ ውጭ የሚከናወን የቅጥር ሂደት ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

7.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ከህግ ደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወኑ ቅጥሮች መ/ቤቱን ተጠያቂ ስለሚያደርገው ትኩረት በመስጠት ማስተካከል ያለበት ሲሆን ለወደፊቱም እንደዚህ ዓይነት ችግሮች እንዳይፈጠሩ የሚመለከተው አካል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

7.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ✓ ቋሚ ሰራተኛ ለመቅጠር ማስታወቂያ ቢወጣም ባለው የደመወዝ መጠን ሰራተኞች ማግኘት ስላልተቻለ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርን በ27/10/2003 እና በ02/13/2004 በማስፈቀድ እንዲቀጠሩ በፈቀደልን መሰረት የተቀጠሩ ናቸው፡፡
- ✓ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሱት ለረጅም ዓመታት ያልተወራረደ ሂሳብ ያለበት በመሆኑና በወቅቱ የነበረው የሂሳብ ስራ በነበረው የደመወዝ መጠን ቋሚ ሰራተኛ ለመቅጠር ባለመቻሉ ነው፡፡

7.4.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የተፈቀደላቸው ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በፊት በ27/10/2003 እና በ02/13/2004 እንደሆነ እና የተቀጠሩትም መመሪያ ከመተላለፉ በፊት በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

7.5 የመ/ቤቱ የሶሻል ክበብ

7.5.1 ግኝት፣

መ/ቤቱ ለሰራተኞች የተመቻቸ የስራ ቦታ መፍጠር እንዲቻል ለሶሻል ክበቡ የቤት፣ የውሃ፣ የመብራት እና የተሽከርካሪ አገልግሎት በነጻ የሰጠ ቢሆንም፡-

1. በ2000 ዓ.ም በተዘጋጀው የሶሻል ክበብ በመተዳደሪያ ደንብ የሽርክና ማህበር ይዘት ያለው በመሆኑ አባል ለመሆን የአባልነት መዋጮ እና በየወሩ ከደመወዛቸው እየተቆረጠ ለክበቡ ገቢ የሚደረግ፣ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የኦዲት ኮሚቴ በሚል የተዋቀረ መሆኑ፡
2. የሶሻል ክበቡ መተዳደሪያ ደንብ የሽርክና ማህበር በመሆኑ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ ደረሰኝ በማሳተም ከሚያገኘው ገቢ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ግብር መክፈል ሲገባው ያለ ንግድ ፈቃድ በሶሻል ክበቡ ስም ደረሰኝ በማሳተም ገቢ የሚሰበስብ ሆኖ መገኘቱ፡

3. የመ/ቤቱ ሶሻል ክበብ ህጋዊ የሰውነት መብት ሳያገኝ አባል ለሆኑት ብቻ የትርፍ ክፍፍል የሚያደርግ መሆኑ፤
4. አባል ያልሆኑ ሰራተኞች ከትርፍ ክፍፍሉ የማያገኙ ስለሆነ በነጻ እኩል ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን መብት ያሳጣ መሆኑ፡፡

7.5.2 <u>ስጋት፤</u>

- ✓ ህጋዊ የሰውነት መብት ሳያገኝ ገቢ ከተሰበሰበ እና ትርፍ ክፍፍል የሚያደርግ ከሆነ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ታክስ ሊያሳጣ ይችላል፡፡
- ✓ መ/ቤቱ ለሰራተኞች የተመቻቸ የስራ ቦታ ለመፍጠር መንግስት በነጻ የተፈቀደለትን የቤት፤ የመብራት፤ የውሃ እና ተሽከርካሪ ተጠቅሞ ከተገኘ ትርፍ አባል ለሆኑት ሰራተኞች ብቻ ማከፋፈል አባል ያልሆኑትን ሰራተኞች መብት ሊያሳጣ ከመቻሉ በተጨማሪ የመንግስትን ንብረት ላልተገባ ጥቅም ሊያውል ይችላል፡፡
- ✓ ከህግ፤ ደንብና መመሪያ ውጪ ያሉ አሰራራሮች ተጠያቂነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

7.5.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

- ➢ መ/ቤቱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለሶሻል ክበቡ ንግድ ፈቃድ በማውጣት ህጋዊ የሰውነት መብት እንዲኖረው በማድረግ የቤት ኪራይ፤ የውሃ፤ የመብራትና የተሽከርካሪ እንዲከፍል ማድረግ ወይም
- ➢ መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻልና መ/ቤቱ ለሶሻል ክበቡ በነጻ የተፈቀዱለትን የቤት፤ የመብራት፤ ውሃ እና ተሽከርካሪ በመጠቀም የትርፍ ክፍፍሉ እንዲቆም በማድረግ ሰራተኞች በተመጣጠነ ዋጋ በመንግስት ሃብት ያልተገባ ጥቅም እንዲኖር ያደረገውን አሰራር በአሳቸኳይ ማቆም ይኖርበታል፡፡

7.5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ✓ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ለወደፊት የሚስተካከል ይሆናል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

8. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፤</u>

8.1.1 <u>ግኝት፤</u>

- በውጭ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፤ ሚሲዮኖች እና የዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 5,375,664.79 በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

- በሰው ሃብት አስተዳደር በተሰጠን መረጃ መሰረት ከ01/02/2008 ጀምሮ በጡረታ ለተገለሉ አንድ ሰራተኛ የጥቅምትና የህዳር ወር 2008 ዓ.ም ደመወዝ በድምር ብር 2364.00 ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ
- የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ተ/ሽ/ቀ5/59 በቀን 29/10/2007 የትምህርት ሚኒስቴር ለ13 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ካፒታል በጀቱን እንዲያስተዳድርለት GIZ-IS ከተባለ ድርጅት ጋር በተደረገው ውል መሰረት በጀቱ በጥቅል ወደ ድርጅቱ እየተላለፈ ክፍያ እንዲፈጽም እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር በስሙ ባሳተመው ደረሰኝ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ተቀናሽ እንዲያደርግ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስብ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን ገልጾ ድርጅቱ ከኮንትራክተሮች ላይ ሰብስቦ ገቢ ያላደረገውን የመንግስት ገንዘብ እንዲሁም በትም/ሚኒስቴር ስም የታተመውን በድርጅቱ ዘንድ የሚገኘውን ደረሰኝ በሙሉ በአስቸኳይ ተሰብስቦ ለኢ.ት/ገ/ጉ/ባለስልጣን ተመላሽ እንዲያደርግ በገለጸው መሰረት አፈጻጸሙን ለማጣራት ገንዘቡ መሰብሰብ በሚገባው ልክ ለመሰብሰቡና የተሰበሰበው ገንዘብ ሁሉ በትክክል ለገቢዎችና ጉምሩክ ገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ቢሞከርም ሂሳቡን ለማጣራት የሚያስችል ሰነዶችንም ሆነ ስለ ሁኔታው በቂ ማብራሪያ ለማግኘት ባለመቻሉ ሂሳቡን ማጣራት አለመቻሉ፡፡

8.1.2 <u>ስጋት፤</u>

- በኦዲት ግኝቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜን ለኪሳራ ሊዳርግ ይችላል፡፡

8.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ የወጣባቸው በመሆኑ በኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን

አባሪ 1

ተ.ቁ	የተከፈለበት ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የክፍያ ምክንያት	የተከፈለው ግለሰብ/ድርጅት	የገንዘብ መጠን
1	06/11/2008	17734	2221103	ዉሃ እና የምሳ	ለጁፒተር ዓለም አቀፍ ሆቴል	419,347.50
2	18/01/2009	19008	2221103	የአልጋ አበል	ቶኩማ ሆቴል	81,022.21
3	29/10/2009	26197	2221103	የቁረስ ፡የምሳ እና የእራት	ቱሪስት ኢንተርናሽናል ሆቴል	105,301.97
4	13/01/2009	18909	2251101	አደራሽ ኪራይ	አባ ገዳ የስብሰባ ማእከል	185120.00
5	13/01/2009	18909	2221103	ሻይ ቡና	አባ ገዳ የስብሰባ ማእከል	468,000.00
9	23/09/2009	0025919	2241101(6251)	ለማስታወቂያ ክፍያ	ለአሜክስ ሚድያ ፕሮሞሽን እና ኮሙኒኬሽን	520,000.00
					ጠቅላላ ድምር	1,778,791.68

አባሪ 2

ተ.ቁ	የተከፈለበት ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የክፍያ ምክንያት	የተከፈለው ግለሰብ/ድርጅት	የገንዘብ መጠን
1	27/06/2009	00027252	2251102	በህንድ ሃገር ለሚማሩ ተማሪዎች	682 ተማሪዎች	6,440,200.80
2	27/06/2009	00027251	2251102	//	//	19,632,861.40
3	27/06/2009	00027249	2251102	//	416ተማሪዎች	2,270,250.00
4	20/08/2009	00028387	//	//	229 ተማሪዎች	1,087,886.80
5	17/04/2009	00025726	//	ሩሲያ	13 ተማሪዎች	21,047,717.76
6	27/06/2009	00027247	//	ህንድ	416 ተማሪዎች	19,198,244.70
7	17/04/2009	0002539	//	//	//	7,629,877.27
8	17/04/2009	00025795	//	//	416 ተማሪዎች	1,195,940.30
9	20/07/2009	00027771	//	ቱርክ	61 ተማሪዎች	1,926,421.69
10	27/06/2009	00027253	//	ህንድ	682 ተማሪዎች	1,368,505.00
11	27/06/2009	00027248	//	//	416 ተማሪዎች	6,247,956.00
12	20/07/2009	00027775	//	//	416 ተማሪዎች	26,334,900.00
13	20/07/2009	00027774	//	ቻይና	305 ተማሪዎች	5,775,715.01

14	28/09/2009	00029119	//	ህንደ	696 ተማሪዎች	28,775,983.60
15	17/04/2009	00025736	//	ፈረንሳይ	20 ተማሪዎች	989,370.43
16	28/09/2009	00029157	//	//	200 ተማሪዎች	714,338.06
17	15/02/2009	0020003	//	ደ/አፍርካ	332 ተማሪዎች	6,747,364.31
					ጠቅላላ ድምር	157,383,533.13

አባሪ 3

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	የሚከናወነው ፕሮጀክት ዓይነት	የውሉ መነሻ ዋጋ	ዉል የተየዘበት ቀን	ቅድሚያ ክፍያው የተከፈለበት ቀን	የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ በ%	የተከፈለው የገንዘብ መጠን
1	ኪዳኔ አክለሉ ጠ.ህ ተቋራጭ	ቤተ-መጻህፍት	28,069,125.02	20/08/2008	14/10/2008	20%	5,613,825.00
2	ቦጋለ ተሰማ ህ.ስ.ተቋራጭ	የተማሪዎች ማደሪያ	23,121,966.40	20/08/2008	6/10/2008	20%	4,624,393.28
3	ኪሮስ ሀድጎ ህ.ስ.ተቋራጭ	የተማሪዎች ማደሪያና የጥበቃ ቤት	23,632,320.53	20/08/2008	9/10/2008	20%	4,726,464.11
4	ሀር ኮንስትራክሽን	ቤተ-ሙከራ እና የተማሪዎች ላውንጅ	18,744,794.76	20/08/2008	6/10/2008	20%	3,748,958.95
5	ቴክሮም ኮንስትራ	ቤተ-ሙከራ	30,239,102.32	20/08/2008	2/10/2008	20%	6,047,820.46
6	ሰቦቃ ወጊ ህ.ስ.ተቋራጭ	የተማሪዎች ማደሪያና የልብስ ማጠቢያ	25,674,050.14	20/08/2008	14/10/2008	20%	5,134,810.03
7	ኦስማን ኦብሶህ.ስ.ተቋራጭ	የማብስያ ቤት፤የመመገቢያ ቤት እና የእንጀራና የዳቦ መጋገሪያ	20,402,333.68	20/08/2008	11/12/2008	20%	4,080,466.74
8	ቲንቲ ኮንስትራክሽን	ሲሚናር	33,088,143.30	20/08/2008	6/10/2008	20%	6,617,628.07
9	ቲንቲ ኮንስትራክሽን	መሰረተልማት	209,618,651.96	05/07/2009	19/08/2009	15%	31,442,798.11
ጠቅላላ ድምር			412,590,488.11				72,037,164.75

አባሪ 4

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የክፍያ ምክንያት	የተከፈለው ግለሰብ/ድርጅት	የተከፈለው የገንዘብ መጠን	ተጨማሪ እሴት ታክስ 15%	መቀነስ የነበረበት 2% ተቀናሽ ግብር
1	27/03□2009	□020342	2241105	የአርማታ ብርት የተጎዝበት	ለፍቃ□ ተኮላ ሀገር ውስጥ ደረጃ 4 የደ/ጭ/ማ/የግ/ት	496,936.36	74,540.45	9,938.73
2	05/01/2009	0018687	//	//	//	210,7□0.48	31,609.57	4,214.61
3	16/12/2008	0018071	//	//	ለግቤ ደረጃ 3 ደ/ተ/ደ/ማ/ማህበር	566,361.50	84,954.23	11,327.23
4	08/04/200□	0020023	//	//	//	193,886.02	29,08□.90	3,877.72
5	30/02/2009	0019905	//	//	//	251,621.86	37,743.28	5,032.44
6	02/06/2009	□021965	/□	//	//	147,963.60	22,194.54	2,959.27
7	06/04/2009	0020629	//	//	ለአስደም ኢንጅነሪንግና ጠ/ን/ኃ/የተ/የግል/ ማህበር	155,667.90	23,350.19	3,113.36
8	20/03/2009	0020224	//	//	//	268,263.80	40,239.57	5,365.28
9	15/03/2009	0020100	//	//	//	453,575.67	68,036.35	9,071.51
□0	15/02/2009	0019573	//	//	//	578,451.60	86,767.74	11,569.03
11	30/01/2009	0019277	//	//	//	1,042,302.12	156,345.32	20,846.04
12	16/12/2009	0018047	//	//	//	397,145.84	59,571.88	7,942.92
13	11/01/2009	0018843	//	//	//	1,098,680.98	164,802.15	21,973.62
14	26/08/2009	0024130	//	//	ኃ/ማርያም ማዘንጊያ የአገር ውስጥ የደ/ጭ/የማመ/የግል ትራንስፖርት	447,012.80	67,051.92	8,940.26
15	08/03/2009	0020017	//	//	//	490,080.17	73,512.03	9,801.60
16	15/04/2009	0020099	//	//	//	511,880.66	76,782.10	10,237.61
17	05/01/2009	0018689	//	//	ለሰሜን ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ1-ሀ የደ/ጭ/ማመ/ባ/ማህበር	156,846.52	23,526.98	3,136.93
18	30/08/2009	0024150	//	//	//	783,137.04	117,470.56	15,662.74
							1,237,581.74	165,010.90

- በሂሳብ መደብ 4201 በተንጠልጣይ ሂሳብ ተይዞ ከ 12 ዓመት በላይ የቆየ ብር 1,774,170.53 መኖሩ፤
- በሂሳብ መደብ 4202 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 2,051,111.31 ከ 12 ዓመት በላይ ሳይተካ የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4274 ከተለያዩ የሂሳብ መደቦች እየዞረ የመጣ እና ሳይወራረድ ከ 13 ዓመት በላይ የቆየ ብር 37,883,977.02 መኖሩ፤

1. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች ላይ በድምሩ ብር 11,882,591.62 ከ1 ዓመት እስከ 10 ዓመት የቆየ እና ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል የቆየ የተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፤